# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 239 ታህሳስ 4 2005 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔ ዘረኞች በአገሩና በማንነቱ ላይ የደቀነበትን የመከራ ቀንበርና ጭቆና ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ በማስወገድ፤ ህዝብ የስልጣን ባለቤት ሆኖ አለም አቀፍ የሲቪክና የፖለቲካ መብቶች የተከበሩባትና ብሄር ብሄረሰበቿ በእኩልነት እጅ ለእጅ ተያይዘዘዉ የሚኖቱባትን ኢትዮጵያን መገንባት የሁላችንም ሀላፊነት ነዉ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የሙስሊም ኢትዮጵያውያን ተቃውሞ በትናንትናው እለትም ቀጥሎ ዋለ፤ ዓላማውም የሙብት ጥያቄው የመላ ሙስሊሙ ህብረተሰብ መሆኑን ለማመላከት ነው ተባለ

ላለፉት አስራ ሁለት ወራቶች በጽናት በመቆም ለሙብታቸው የሚያደርጉትን እልህ አስጨራሽ ትግል እያካሄዱ ያሉት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ትግላቸውን አጠናክረው በመቀጠል በትናንትናው እለትም ድምጻቸውን ሲያሰሙ መዋላቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ ገለጸ።

እነኝሁ ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን በትናንቱ ተቃውሞአቸው ድምጻችን ይሰማ፣ እንዲሁም የታሰሩ መሪዎቻችን ይለቀቁ፣ በማለት በከፍተኛ ሁኔታ ድምጻቸውን ሲያሰሙ መዋላቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በትናንትናው እለት የወያኔ አገዛዝ ፖሊሶች እጂግ በብዛት በመሆን ተቃውሞውን ለማጥፋት ቢሞክሩም ሳይሳካላቸው እንደቀረ ታውቋል።

ይሁን እንጂ ዘጋቢያችን ያይን እማኞችን ዋቢ በማድረግ በላከልን ዘገባ ከሃያ በላይ የሚሆኑ ሴቶችን የጨካኙ ወያኔ አገዛዝ ፖሊሶች በሴቶች መስገጂያ በኩል በመግባትይዘው ማሰራቸው ታውቋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የኢዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደዘገበው የትናንቱ ተቃውሙ ሀይለማርያም ደሳለኝ በቅርቡ ለአልጀሪያ ቴሌቪዥን የሙስሊሙን ጥያቄ በተመለከተ የሰጠውን ቅጥፈት የተሞላበት ቃለምልልስ ለመቃወም ያለመ ነው። እንደ ኢሳት ዘገባ ሐይለማርያም በሙስሊሞች ጥያቄ ዙሪያ ለቀረበለት ጥያቄ፣ የሙስሊሙ ጥያቄ የጥቂቶች መሆኑንና አብዛኛው ሙስሊም መብቱ ተከብሮለት እየኖረ መሆኑን ተናግሮ እንደነበር ገልጿል።

## የዘረኛው አገዛዝ ፌዴራል ፖሊስ አገሪቱን በስለላ ካሜራዎች ለማጥለቅለቅ ማቀዱ ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ከፌዴራል ፖሊስ የተገኘው መረጃ በመጥቀስ እንዳመለከተው በኢትዮጵያ የፖሊስ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስአበባ ዋናዋና መንገዶች ላይ ካሜራዎችን በመግጠምና የመቆጣጠሪያ ክፍል በማቋቋም በመንገዶቹ ላይ የሚካሄዱ ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች ሲቆጣጠር እንደቆየ ገልጿል፡፡

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከአንዳንድ የጥቅም ተካፋይ ከሆኑ ሃገራት ጋር በመተባበር በስልጣን ላይ ሊቆይ የሚችልባቸውን አጋዥ ቴክኒዮሎጆች ጥቅም ላይ ሲያውል መቆየቱ በስፋት የሚታወቅ ሲሆን እነዚህም ዘመናዊ ካሜራዎች ዋንኛ ጥቅማቸው ወያኔ ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊያንን ለመሰለል ብሎም አፍኖ ለመግዛት ካለው ጥልቅ ፍላጎት ጋር የተያያዘ መሆኑ በርካቶች ይስማሙበታል።

እጂግ አብዛኛው ህብረተሰብ በድህነትና በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ባለበት ሁኔታ አረመኔው አገዛዝ እጂግ በራካታ ሚሊዮን ዶላር እያፈሰሰ በስልጣን ላይ ሊቆይ የሚችልባቸውን መንገዶች በማመቻቸት ስራ ላይ ተጠምዶ እንደቆየ በስፋት መዘገቡም ይታወሳል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደገለጸው ፌዴራል ፖሊስ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመታገዝ የሚፈጸሙ የሳይበር ወንጀሎችን ለመከታተልና አጥፊዎችን ለመያዝ ቢሮ ከፍቶ እየሰራ መሆኑን ማስታወቁን ገልጾ አንድ የፖሊስ መኮንን የወያኔው አገዛዝ በኢንተርኔት በሚደረጉት ትግሎች ተደናግጧል፣ በአገሪቱ የለውጥ ፍላጎት እያየለ መምጣቱ አስደንግጦታል። በዚህም የተነሳ ሁሉንም ነገር ለመቆጣጠር ይፈልጋል ማለታቸውን ገልጿል።

## የአሜሪካን አምባሳደሯ ሱዛን ራይስ ራሳቸውን ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር እጩነት ማግለላቸው ተዘገበ

በተባበሩት መንግሥታ የአሜሪካ አምባሳደር የሆኑትና በፕሬዚዳንት ኦባማ ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የውጭ ጉዳይ ሚ/ር መስሪያቤትን እንዲመሩ ሊታጩ ይችላሉ የተባሉት ቀዳሚ ተወዳዳሪ ሱዛን ራይስ ራሳቸውን ከእጩነት አግልለዋል፡፡ ጉዳዩ ለፕሬዚዳንቱ የፖለቲካ ክስረት፤ ምርጫውን ሲቃወሙ ለነበሩት የሪፓብሊካን ፓርቲ አመራሮች እና በአሜሪካ ለሚገኙ ኢትዮጵያውን ታላቅ ድል ሆኗል፡፡

የቤንጋዚው መዘዝ በሱዛን ራይስ ሰለባነት የሚጠናቀቅ ብቻ ሳይሆን እየቆየ በርካታ ምስጢሮች የሚጋለጡበት እንደሚሆን ተንታኞች ይተነብያሉ፡፡ የአምባሳደሯ ውሳኔም የሸፍንፍኑ አንዱ ገጽታ እንደሆነም ይናገራሉ፡፡ ሱዛን ራይስም ሆነ ሌላ ግለሰብ በሚ/ር ቦታው ላይ ቢሾም በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ እምብዛም እንዳልሆነ ባለፉት አስተዳደሮች የታየ ጉዳይ ነው፡፡ ጎልጉል የድረገጽ ጋዜጣ በዚህ ረገድ ከፍተኛውን የመወሰንና ፖሊሲ የማውጣት ኃላፊነት የወደቀው በሕዝብ አንድ እምብዛም በማይታወቁት የሦስትዮሹ ኮሚሽን (trilateral commission) እና የውጭ ግንኙነት ምክርቤት (council on foreign relations) መሆኑን ከዚህ በፊት መዘገቡ ይታወሳል፡፡

አምባሳደር ራይስ መልቀቂያቸውን ካቀረቡ በኋላ በአሁኑ ጊዜ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ቀዳሚ እጩ እንደሆኑ የሚነገርላቸው ሴናተር ጆን ኬሪ የሪፓብሊካኑ ግልጽ ድጋፍ የተሰጣቸው በመሆኑ በቀላሉ የሕግመወሰኛ ም/ቤቱን ድምጽ እንደሚያገኙ ተነግሯል፡፡ ፕሬዚዳንት ኦባማ ግን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ማንን በእጩነት እንደሚያቀርቡ እስካሁን ይፋ አላደረጉም፡፡

## ኦህዴድ አባላቱ ዉስጥ የተፈጠረዉን ስር የሰደደ ክፍፍል ለማብረድ ስብሰባ ጠራ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ከኦህዴድ አባላት የመጣበትን ከፍተኛ ተቃዉሞ ለማቀዝቀዝ ሙክታር ከድርን በምክትል ጠ/ሚኒስትርነት ማዕረግ የይስሙላ ሹመት ቢሾመዉም “ከአሁን በኋላ መታለል በቃ” ብለዉ የተነሱት የኦህዴድ አባላት በተለይ በምስራቅ ኦሮሚያና በሀረሪ ክልል የሚገኙ በመካከለኛ ደረጃ የሚገኙ የኦህዴድ አመራሮች ፣ መምህራን፤ ርእሰ መምህራንና የወረዳ አስተዳዳሪዎችና አሁንም የተቃዉሞ ድምጻቸዉን እያሰሙ መሆኑን ከወደ ኦሮሚያ ክልል የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። ይህንኑ ኦህዴድ ዉስጥ የተፈጠረዉን ችግር ለማብረድ በሚል የድርጅቱ አባላት ከህዳር 27 ጀምሮ በሀረሪ ክልል በአሚር አብዱላሂ አዳራሽ መጋቢት 28፣ ቀን 2005 ዓም በኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት በአቶ ረጋሳ ከፍያለው ሰብሳቢነት ስብሰባ የተቀመጡ ሲሆን በምስራቅ ሀረርጌ ደግሞ መካከለኛ አመራር፣ ርእሰ መምህራንና የድርጅት አባላት የተሳተፉበት ተመሳሳይ ስብሰባ በነጋታዉ ተጀምሯል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ በዩኒቨርሲቲዎችና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ኢህአዴጋዊ ስልጠና ሊሰጥ ነዉ ተባለ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ለሁለተኛ ደረጃ፤ ለመሰናዶ፤ ለኮሌጅና ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚሰጥ ከፍተኛ የስልጠና ፕሮግራም ማዘጋጀቱን ኢሳት ዉስጥ አዋቂ ምችጮችን ጠቅሶ ዘገበ። በመርሀ ግብሩ መሰረት ከተጠቀሱት የትምህርት ተቋማት የሚመረጡ ቁልፍ ተማሪዎች በቅድሚያ ስልጠና ከተሰጣቸው በኋላ እነዚሁ ሰልጣኞች ተመልሰው በመሄድ ለተቀረው ተማሪ ስልጠና ይሰጣሉ።ስልጠናው የሚቆየው ለአንድ ሳምንት ሲሆን፣ የሚሰለጥኑበት ሁኔታም በአብዛኛው ኢህአዴግ ባለፉት ስምንት አመታት ስላስገኛቸው ድሎች፣ ስለርእዮተ አለምና፤ ስለእስልምና አክራሪነት እንደሆነ ታዉቋል።

የዚህ ስልጠና ትኩረት በመጪው የካቲት ወር የሚካሄደው የወረዳ ምርጫ መሆኑን ምንጮቻችን ገልጸዉ በአሁኑ ግዜ ወያኔ ጧትና ማታ የሚሰራዉ በቅርቡ የተዘረጋውን የአንድ ለአምስት አደረጃጃት በስፋት ወደ ነዋሪው ለማዳረስ እንደሆነ ታዉቋል።በተለያዩ መስሪያ ቤቶች የሚገኙ ሰራተኞች በአንድ ለአምስት አደረጃጀት በመወጠራቸው ሌሎች ጉዳዮችን እንዳያስቡ እየተደረጉ መሆኑን ብዙ ሰራተኞች በመናገር ላይ ናቸዉ።ሠራተኞች በየእለቱ ከቀኑ 10 ሰአት ጀምረው ስለ መስሪያ ቤታቸው የስራ እንቅስቃሴ ለአንድ ለአምስት ሰብሳቢው ሪፖርት ማድረግ የሚያደርጉ ሲሆን፤ ሰብሳቢውም እንደዚሁ ለበላይ አለቃው መረጃዎችን በማስተላለፍ ገዢው ፓርቲ አጠቃላይ ፖለቲካ እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር እንዲያመቸው ማድረጉን ሰራተኞች ገልጸዋል።

## አሸባሪው ወያኔ ህዝብን እያሸበረ ነው

ወያኔን አንፈልግም፣ ወያኔን አንደግፍም እንዲሁም ከወያኔ ጎን አንቆምም በማለት በጽናት የሚታገሉ ኢትዮጵያዊያንን አሸባሪ ናችሁ የሚል ታፔላ በመለጠፍ የሚታወቀው አሸባሪ አገዛዝ ሰሞኑን ጅጅጋ ውስጥ በሚገኙ የሆቴል ባለቤቶች ላይ ግፈኛ ቅጣት መጀመሩን ዘጋቢያችን የጂጂጋ ነዋሪዎችን ዋቢ በማድረግ በላከልን ዘገባ ላይ አመለከተ። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት የጂጂጋ ሆቴሎች ባለቤቶች የመቀጫ መአት እየወረደባቸው ያለው በሆቴሎቻችሁ አሻበሪዎችን ታስድራላችሁ በሚል ሽፋን ነው። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ውሸት ሲደጋገም...

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ለ7ኛ ግዜ የሚያከብረዉን የብሄር-ብሄረሰቦች ቀን የኢትዮጵያ ህዝብ ዕጽዋት በመትከል ትርጉም የለሹን ህገ-መንግስት አጠንክሮ እንዲጠብቅ የአምባገነኑ አገዛዝ ሃላፊዎች እየተናገሩ ነው:: ወያኔ የሚናገረዉና የሚሰራዉ እጅግ በጣም የሚቃረን ድርጅት መሆኑ ለማንም የተደበቀ አይደለም፤ ለምሳሌ የኢትዮጵያን የፖለቲካና የኤኮኖሚ መዋቅሮች ብቻዉን ሙሉ በሙሉ እየተቆጣጠረ በአንድ በኩል ሀየማንነትና የእኩልነት ጥያቄዎች በህገ-መንግስቱ ምላሽ አግኝተዋል ይላል በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን የተረጋገጠ እኩልነት ሲያሳየን የሚፈልገዉ ብሔር ብሔረሰበፐችን ሰብስቦ ዝፈኑ በማለት ነዉ::

ባለፉት 21 አመታት ኢትዮጵያ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ዜጎቿ ቁጥር በእጥፍ እየጨመረ እና በተለይም በገጠር የሚኖረው አርሶ አደር ገበሬ መሬቱ፣ ባህሉና ነጻነቱ እየተነጠቀ ለውጭ ባለጸጋዎች እየተቸበቸበ ባለበት ወቅትናት፤ በአገሪቱ የወልና የግል መብት ባልተከበረበት ሁኔታ ለይስሙላ ህዝብን በአደባባይ አስወጥቶ ማስጨፈር፣ ህዝብን ማታለልና በአገር መቀለድ ነው።

የብሄር-ብሄረሰቦች መብት የሚከበረው ወይም መከበር የሚጀመረው የግለሰብ ሁለንተናዊ መብት ሲከበርና ኢትዮጵያ ዉስጥ ፍትህ፤እኩልነትና ነፃነት ሲሰፍኑ ብቻ ነዉ። እነዚህ ሁሉ በሌሉበት፤ ግልሰቦች እየታሰሩ ግፍና ሰቆቃ እየተፈጸመባቸዉና ብሔር ብሔረሰቦች ደግሞ የፖለቲካ ስልጣን ተነፍገዉ የበይ ተመላካች ሆነዉ እየታየ ይህ በየአመቱ ህዳር በመጣ ቁጥር የምናየዉ የብሔር ብሔረሰቦች ሆይ ሆይታና ከበሮ ድለቃ የሚያስታውሰን የደርግ ስርዐት ሲያደርግ የነበረውን የአቢዎት በዓል አከባበር ነዉ።

በአንድ ወቅት የወያኔ አምባገነኖች "የአክሱም ሐውልት ለአማራውና፣ ለወላይታው ምኑ ነው?" እያሉ በአገራችን ታሪካዊ ቅርሶች ላይ ሲያፌዙ የነበሩት የወያኔ ዘረኞች ዛሬ ምን እየታያቸው ወይምእየሸተታቸው ይሆን ስለ ብሄር ብሄረሰብ የተቆረቆሩ የሚመስሉት የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀርም።

የጋምቤላ፣ የኦጋዴንና የታችኛው ኦሞ ወገኖቻችን መሬታቸውንና ባህላቸውን ተነጥቀው እየተሰደዱና እየተገደሉ ባሉበት አገር ኑናና ስለ ብሔር ብሄረሰቦች መብት መከበር ጨፍሩ መባሉ ከቶ አስተዛዛቢ ነው። በተለይም የአንድ ብሄር የበላይነት ስር ሰዶ በነገሰባት ኢትዮጵያ ዛሬ ለይስሙላ ለማስመሰል የሚደረግ ሩጫ መቆም ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ ህዝብን በብሄር ብሄረሰብ ስም ጭፈራ ማታለል ይብቃ! የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግለሰብና የወል መብቱ፤ነፃነቱና እኩልነቱሊከበርለት ይገባል። የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ እጦት በአለባት ሀገራችን፤ አምባገነኖች በህዝብ ስም የሚነግዱትን የማስመሰል ንግድ እና ውሸት በአስቸኳይ ተባብረን ልናስቆመው ተገቢ ነው።

ኢትዮጵያ ከ80 በላይ በሚሆኑ ብሄር ብሄረሰቦች አገር መሆኗ መሆኗ እየታወቀ በአንድ ብሄር የበላይነት ዙሪያ ያጠነጠነ ፌዴራሊዚም ፈጥሮ እራስን ፈላጭ ቆራጭ ሌሎችን ሌሎችን ተመልካች እንዳደረጉ መቀጠል በዛሬዉ መረጃ በነገሰበትና የለዉጥ ማዕበል አለማችንን ባጥለቀለቀበት ዘመን ከቶዉንም ሊታሰብ የማይችል የአምባገነኖች የቀን ህልም ነዉ። ዛሬ የኢትዮጵያ ብሔር ብሄረሰቦች ባስቸኳይ የሚያስፈልጋቸዉ በአካባቢያቸዉ እራሳቸዉን ካለምንም ተፅዕኖ ማስተዳደርና በማዕከል ደግሞ የፖለቲካ ስልጣንን ተጋርተዉ በእኩልነት መኖርን ነዉ፤ የፌዴራል ስርዐት አወቃቀርም የሚለዉ ይህንን እንጂ ተሰብስቦ መዝፈንን አይደለም።

ለብዙ ዘመናት ተከባብሮና ተሳስቦ የኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ ያለመታደል ሆኖ ዛሬ አንተ አማራ፣ አሮሞ፣ ትግሬ፣ከንባታ... እየተባለ መታወቂያው የብሄር ማንነቱ ሆኖ አሳፋሪ ኑሮ እየኖረ ነው። ይህን ሀቅ ደብቆና ህዝብን አታሎ፣ አፍኖና ጨቁኖ አደባባይ ውጥታችሁ ስለብሄር መብት መከበር ከበሮ ደልቁ የሚለውን የወያኔ በማር የተለወሰ መርዝ የኢትዮጵያ ህዝብ በደንብ ሊረዳውና አምርሮ ሊታገለዉ ይገባል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔ ዘረኞች በአገሩና በማንነቱ ላይ የደቀነበትን የመከራ ቀንበርና ጭቆና ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ በማስወገድ፤ ህዝብ የስልጣን ባለቤት ሆኖ አለም አቀፍ የሲቪክና የፖለቲካ መብቶች የተከበሩባትና ብሄር ብሄረሰበቿ በእኩልነት እጅ ለእጅ ተያይዘዘዉ የሚኖቱባትን ኢትዮጵያን መገንባት የሁላችንም ሀላፊነት ነዉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

## የአዲስ አበባ ወጣቶች የቃሊቲ ጉብኝት ዝግጅት በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑ ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደዘገበው በመጪው እሁድ ታህሳስ 7፣ 2005 ዓም አለአግባብ የታሰሩ የሙስሊም ማህበረሰብ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን፣ ጋዜጠኞችንና የተቃዋሚ መሪዎችን በቃሊቲ ተገኝተው ለመጠየቅ የወጠኑት እቅድ ጥሩ ምላሽ እያገኘ መምጣቱን አዘጋጆች ገልጸዋል ብሏል።

እንደ ኢሳት ዘገባ ማንኛውም የህገመንግስቱን የእምነት እና ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት መከበር እንዳለበት የሚደግፍ ኢትዮጵያዊ በሙሉ ወደ ቃሊቲ በመሄድ ድጋፉን እንዲያደርግ እንጠይቃለን የሚል መግለጫ ካወጡ በሁዋላ ጥሪው በማህበራዊ ድረገጾች ከመሰራጨት አልፎ በአዲስ አበባም ህዝቡ እየተነጋገረበት ነው ብሉዋል።

መላው ህዝባቸውን ሲያገለግሉ የነበሩ የሰላም እና የነጻነት ታጋዮች በእስር ቤት እየማቀቁ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዝም ብሎ የሚመለከት ከሆነ የታሪክ እና የትውልድ ተጠያቂነት ይኖርበታል በማለት አዘጋጆች መግለጻቸውን ኢሳት አያይዞ ዘግቧል።

ሀሳባቸውን በመግለጻቸው ብቻ በርካታ ኢትዮጵያውያን በግፍ እስር ላይ እንደሚገኙ የገለጡት አዘጋጆች፣ የሙስሊም መሪዎችን ጨምሮ ፖለቲከኞችን አቶ አንዱለአም አራጌን፣ ከንፈሚካኤል ደበበ ( አበበ ቀስቶ)፣ ምትኩ ዳምጤ፣ ናትናኤል አለሙ፣ በቀለ ገርባ፣ አልባና ሊሌሳ፣ ጋዜጠኞችን እስክንድር ነጋ፣ ርእዮት አለሙ፣ ውብሸት ታየና ሌሎችንም የህሊና እስረኞች የመጠየቅ ፍላጎቱ አላቸው።

አረመኔው የወያኔ አገዛዝ የስልጣን ወምበርን ከተቆናጠጠበትና በተለይም ከ1997 ምርጫ በኋላ ለሚገጥሙት የህዝብ ተቃውሞዎች ተቃዋሚዎችን በግፍ ወደ እስር ቤት ማጎርና ማሰቃየት፣ እንዲሁም የተወሰኑትን እስከ መግደል የሚደርስ ርምጃ እየወሰደ ያለ ዘረኛ አገዛዝ እንደሆነ በስፋት ሲዘገብ መቆየቱ ይታወሳል።

ከአምባገነኑ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በኋላም ቢሆን ለይስሙላ የተሾመው ሀይለማርያም ደሳለኝ በእስር ላይ የሚገኙት ኢትዮጵያዊያን አሸባሪዎችና ከአሸባሪዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው እንጅ የህሊና እስረኞች አይደሉም በማለት ከአልጀዚራ የዜና አውታር ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ

## አህዴድ አባላቱ ዉስጥ የተፈጠረዉን ስር የሰደደ .

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በዚህ ከ700 በላይ የሚሆኑ የኦህዴድ አባላት በተሳተፉበት ስብሰባ ዋነኛ የመወያያ ርዕስ ሆነው ከቀረቡት መካከል በድርጅቱ ውስጥ የተፈጠረው ልዩነትና የሙስሊሙ እንቅስቃሴ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ በስብሰባዉ ላይ የኦሮሞ ህዝብ በብሄር ብሄረሰቦች ቀን ማንነቱን ያስከበረ መሆኑ፤ ኦነግ የሚያቀነቅነው የመገንጠል ሀሳብ በአንቀጽ 39 የተከበረ መሆኑና በአመራሩ መካከል የታዩ ክፍተቶች የተዘጉ መሆናቸዉ ተደጋግሞ ተስተጋብቷል። ከዚህ በተጨማሪ "የኦነግ አመለካከት ያላቸው ሰርጎ ገቦች" በቂ የስልጣን ቦታ አላገኘንም በማለት የሚያስወሩት ሀሰት መሆኑንና ኦህዴድ የምክትል ጠ/ሚኒስትርነት ስልጣን ማግኘቱን የስብሰባዉ መሪዎች በተደጋጋሚ ሲናገሩ ተደምጠዋል። በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛዉ የስብሰባዉ ተሳታፊ " ይህ በቂ አይደለም " ምስራቅ ሀረርጌ በኦሮሚያ ክልል ስር መሆን ሲገባው በሀረሪ ክልል ሆኗል፣ ቋንቋችን ተግባራዊ ይሁን ከተባለ በኋላ እስካሁን ተግባራዊ አልሆንም።" ወያኔንና ለወያኔ የደሩትን የኦህዴድ መሪዎች ያስቆጣ ጥያቄ አቅርበዋል።

## አሸባሪው ወያኔ ህዝብን እያሸበረ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘረኛውና አሸባሪው የወያኔ አገዛዝ በተለያዩ አቅጣጫዎች ለረጂም አመታት የተፈጠረበትን ውጥረት ለማርገብ የተለያዩ ሚስጥራዊና ይፋ ርምጃዎችን ለመውሰድ ቢሞክርም እስካሁን ድረስ ፍጹም ሊሳካለት እንዳልቻለ የሚታወቅ ሲሆን፣ ሙከራዎቹ ሁሉ ሲከሽፉበት አሁን ደግሞ ፊቱን ወደ ከተማ ነዋሪው ህብረተሰብ ማዞሩንና ህዝብንም ማሸበሩን መቀጠሉን ዘጋቢያችን አያይዞ በላከልን ዘገባ ገልጿል።

አረመኔው የወያኔ አገዛዝ የከተማ ነዋሪዎቹን በመቅጣት ብቻ ሳያቆም፣ ሚሊሺያዎቹን በተለያዩ ቦታዎች በማሰማራት ሆቴሎችንና ሌሎችንም የንግድ ተቋማት እንዲዘርፉ እያደረገ መሆኑን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንድ ተጎጂ የሆቴል ቤት ባለቤት እንደተናገሩት፣ ወያኔ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር በከተማዋ የሚገኙት ነዋሪዎች እጂግ እንዲማረሩ እያደረገ ነው ካሉ በኋላ፣ ወያኔ እንዲህ አይነት ማንገላታት ስላደረሰብን ብቻ አጎብድደን የምንገዛበት ምንም ምክንያት የለም፣ እንዲያዉም የበለጠ እንድንጠነክርና ይህን ዘረኛ አገዛዝም በጽናት እንድንፋለመው ያነሳሳናል ብለዋል።

# ሦስቱ ባዶ ወንበሮች

ኤፍሬም እሸቴ

ወንበር እና ዙፋን ብዙ መገለጫ አለው። ወንበር ሲባል ሁላችን ራሳችንን የምናሳርፍበት ማንኛውም መቀመጫ ማለት መሆኑ እንዳለ ሆኖ "ወንበር" ብዙ አንድምታ እንዳለው እናውቃለን። ለምሳሌ ፍርድ ቤት ገብተን "የግራ ወንበር፤ የቀኝ ወንበር" ሲባል ብንሰማ ትርጉሙ "የግራ ዳኛ፣ የቀኝ ዳኛ" መሆኑ ይከሰትልናል። ምናልባት ወደ አብነት ት/ቤት (ቆሎ ት/ቤት) ጎራ ብለን "ወንበር ተዘርግቷል፤ ወንበር ታጥፏል" ሲባል ብንሰማ "ትምህርት ተጀምሯል፣ ትምህርቱ ተጠናቋል" ማለት ነው። "እገሌ ወንበር ተከለ" ከተባለ ደግሞ "መምህር ሆነ፣ አንድ የትምህርት ዘረፍ ለማስተማር ጀመረ" ማለት ይሆናል። ሥልጣን ባለበት አካባቢ "እገሌ የእገሌን ወንበር ይፈልጋል" ከተባለ .... ያው ... ሥልጣንም ከሆነች፣ ኃላፊነትም ከሆነች ... ሊቀማ የተዘጋጀ አለ ማለት ነው።

## አንድ ታሪክ

እዚህ በአሜሪካ የምርጫ ፉክክር ሰሞን ሁለት ታላላቅ የፓርቲዎቹ ጉባዔያት ተካሂደው ነበር። የሁለቱም ፓርቲዎች ዓመታዊና ፕሬዚዳንታዊ እጨዎቻቸውን የሚያጸድቁባቸው ወሳኝ ጉባዔዎች። ታዲያ፣ ከሁለቱ በአንዱ፣ በሪፐብሊካን ዓመታዊ ጉባዔ ላይ "ራምኒን ለማስተዋወቅ፣ ተመራጭ ለማድረግ" የቀረቡት ዝነኛው የሆሊውድ ኮከብ ክሊንት ኢስትዉድ (**Clint Eastwood**) ንግግራቸውን ሆሊዉዳዊ ድራማ አስመስለው ቀርበዋል። ሰውየው በንግግራቸው ጣልቃ፣ ከፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ጋር ክርክር ቢጤ ያደረጉበት ትዕይንት አስደማሚ ነው። በርግጥ ኦባማ በቦታው አልነበሩም። እርሳቸውን እንዲተካ የተደረገው ገጸባሕርይ "ባዶ ወንበር" ነበር። ኢስትዉድ ሲያወሩ ወደ ወንበሩ እየዞሩ "እንደ ሰው" እያናገሩት ነበር። እናም በትዕይንቱ የተሳለቁ ሰዎች "Obamachair" የሚል ቃል ፈጥረው ObamaCare የሚለውን ለውጠው) ሲዘባበቱባቸው ሰንብተዋል። "ካረጁ አይበጁ" እያሉም አሹፈውባቸዋል። ወደ ኢንተርኔት ገባ ብላችሁ "ኦባማቼር" ብትሉ ጉዱን ታዩታላችሁ።

## ሌላ ታሪክ

እንዲህ በዐቢይና ታላቅ ጉባኤ ላይ በክብር የሚቀመጥ "ባዶ ወንበር" የማውቀው በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅ/ሲኖዶስ ጉባዔ ላይ ነው። ጉባዔው በፓትርያርኩ መሪነት የሚስተናበር ቢሆንም መሪውና ወሳኙ መንፈስ ቅዱስ ነው ከሚለው አስተምሮ በመነሣት በጉባዔው ውስጥ በመጎናጸፊያ የከበረ አንድ ባዶ "ዙፋን" እንደሚቀመጥ አባቶች ይናገራሉ። ወንበሩ ከርዕሰ ጉባኤው፣ ከጉባዔው ሊቀ መንበር፣ ከፓትርያርኩ ጀርባ ይቀመጣል። ማንም ሰው አይቀመጥበትም። መንፈስ ቅዱስ የጉባዔው አካልና መሪ መሆኑን ያጠይቃል። "ባዶው ወንበር" ተምሳሌታዊ ብቻ ሳይሆን አማናዊ ትርጉም ያለው ሐሳብ ነው። በሌሎቹ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትም ይሁን ሲኖዶሳውያን በሆኑ ካቶሊክን በመሳሰሉ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህ ትውፊት ይኑር አይኑር አላወቅኹም።

የአቶ ኢስትዉድ ባዶ ወንበር እና ሃይማኖታዊ ትርጓሜ ያለው የቤተ ክርስቲያን "ባዶ ዙፋን" በይዘትም፣ በተምሳሌትም ይለያያሉ። የመጀመሪያው "ወንበር" ለጊዜው በዚያ ቦታ ያልተገኘ ሰውን ወክሎ እንዲጫወት የተደረገ ገጸ ባሕርይ ሲሆን ሁለተኛው ግን በርግጥም "እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በመካከላችን አለ፤ ይመራናል" ብሎ በማመን የሚደረግ ነው።

## ሦስተኛ ታሪክ

ታዲያ የባዶ ወንበር ነገር ለሦስተኛ ጊዜ ራሴን "ቂው" ያደረገኝ አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ም/ቤት ተገኝተው መልስ ሲሰጡ የተቀመጡበትን ቦታ ባየኹ ጊዜ ነው። "ምናልባት አቀራረጹ ይሆን?" ብዬ አተኩሬ ለማየት ሞከርኩ። በርግጥም አቶ ኃ/ማርያም የተቀመጡበት ቦታ የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር በሚቀመጡበት ቦታ አልነበረም። የአቶ መለስ "ወንበር" (ሁለተኛው ተርታ ቁጥር አንድ) ባዶዋን ቁጭ ብላለች። ደርሶ ተቼ፣ ደርሶ ነቃፊ ላለመሆን ለራሴ ሁሉንም ሎጂካዊ አመክንዮዎች ለማየት ሞከርኩ። በዚህም ብል በዚያ ያቺ "ወንበር" ባዶ የሆነችበት ምክንያት ግልጽ አልሆነልኝም። መቼም እንደ አቶ ኢስትዉድም፣ እንደ ቅ/ሲኖዶሱም እንዳልሆነ እናውቀዋለን። ታዲያ ለምን ባዶ አደረጓት?

በየትኛውም የሥልጣን ወንበር ላይ ለሚቀመጥ ሰው፣ እርሱ በሚያልፍበት ጊዜ ተተኪው በርሱ ቦታ እንደሚቀመጥ፣ እንኳን ዛሬ "ዲሞክራሲያውያን" ነን ብለን ቀርቶ በነገሥታቱም የተለመደ ነው። "ተቀመጥ በወንበሬ፣ ተናገር በከንፈሬ" እንዲል "መተካካቱ" ሲመጣ ከነሙሉ ክብሩና ግዴታው ሁሉ እንጂ በግማሹ አይደለም። ጠቅላይ ሚኒስትር የመተካት ልምድ የሌላት አገራችን እርሟን ከዚያ ሰዓት ስትደርስ የትኛውን ጥላ የትኛውን እንደምታንጠለጥል የቸገራት ይመስላል። በሌሎች ጉዳዮች ሲሆን "በሕንድ እንዲህ ሲደርግ ዓይተን ነው፣ ጎረቤታችን ኬኒያ እንኳን እንዲህ ነው የምታደርገው፣ ብዙ ቋንቋዎች የሚነገሩባት ስዊዘርላንድ እንዲህ ናት" እንደሚባለው በዚህ ጉዳይ ማጣቀሻ ለመፈለግ የተሞከረ አይመስልም።

በመጀመሪያ። የጠ/ሚኒስትሩ ቤተሰቦች ቤተ መንግሥቱን ለአዲሱ ጠ/ሚኒስትር ላለማስረከብ "ግብግብ" መግጠማቸውን "ጠላት የሚባለው ዳያስጶራው" ብቻ ሳይሆን "የታመኑ የውጪ አገር ፈረንጅ ጋዜጠኞች" ሳይቀሩ ሲተቹ ሰንብተዋል። እንደ መንግሥት ሳይሆን እንደ ግለሰብ ሳስበው እንኳን 20 ዓመት 2 ዓመት ከምኖርበት አፓርታማ ስቀይር እንዴት እንደሚከብድ አውቀዋለኹ። "ይኼ ሁሉ ዕቃ መቼ የሰበሰብኩት ነው?" ማለት የተለመደ ነው "ልሸክፍህ" ሲሉት። የሆነው ሆኖ የቤት ርክክቡ "ሰላማዊ" በሆነ መንገድ መጠናቀቁ ተገቢም፣ የሚጠበቅም ነው።

ቤቱ ይለቀቅ እንጂ፣ እንደማንኛውም የመሪ ቤት "የሚነቃነቁ" እና "የማይነቃነቁ" ነገሮች መኖራቸው ይታወቃል።

መተካካት ስለተባለ ብቻ ኋላ የመጣው የፊተኛውን ጫማና ኮት አድርግ አይባልም። የፊተኛው ሲጠቀምባቸው ከነበሩት ዕቃዎች መካከል ለመታሰቢያነት በሙዚየም ሊቀመጡ የሚገባቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። አገሪቱን 20 ዓመት ያስተዳደሩት ጠ/ሚኒስትር (እንደተባለው በስማቸው ሙዚየም የሚቆም ከሆነ) ይጠቀሙባቸው የነበሩት የቢሮ ዕቃዎች ወዘተ ወዘተ መሰብሰባቸው አይቀር ይሆናል።

ይሁን እንጂ አዲሱ ጠ/ሚኒስትር መንግሥታዊ ኃላፊነትን በሚረከቡበት ወቅት ከነሙሉ ክብሩ እንጂ በጎዶሎነት መሆን አይገባውም። በፓርቲ ሥርዓታቸው ለቀድሞ የፓርቲ ሊቀመንበራቸው ክብር ሲሉ የፓርቲያቸውን "ወንበር ባዶ" ማድረግ ይችላሉ። የመንግሥት ሥልጣን ግን አገራዊ እንደመሆኑ ለግለሰቡ የሚሰጠው ክብር የሰውየውን ማንነት ከግምት ውስጥ ሳያስገባ መሆን አለበት። እውነቱን ለመናገር የፓርላማው ባዶ ወንበር ከቀጥተኛ ትርጉሙ ይልቅ ተምሳሌታዊነቱ (Symbolism) የበለጠ ትርጉም ይሰጠኛል። አቶ ኃ/ማርያም በመለስ ወንበር አለመቀመጣቸው ብቻ ሳይሆን ያልተረከቡት ሌላም ብዙ ነገር እንዳለ ማሳያ ይመስላል። ቢሯቸውስ "ግዴለም የድሮው ቢሮዬ ሆኜ እሠራለኹ" ወይም "አንዲት ወንበር በጎን በኩል አስቀምጡልኝ" ብለው በደባልነት ገብተው ይሆን?

## "ከልት"/Cult መፍጠር

ሳስበው ሳስበው መለስን "ኢትዮጵያዊው ኪም ኤል ሱንግ" ለማድረግ እየተሠራ ይመስለኛል። ኪም ኤል-ሱንግ እ.ኤ.አ. ከ1948-1994 ድረስ የአገሪቱን አመራር ጨብጠው የዘለቁ መሪ ነበሩ። ከ1948-1972 ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ከ1972-94 ደግሞ ፕሬዚዳንት ነበሩ። እርሳቸው በሥልጣን ላይ ብቻቸውን በተቀመጡባቸው ዓመታት አሜሪካ 10 ፕሬዚዳንቶችን፣ እንግሊዝ 14 ጠ/ሚኒስትሮችን፣ ሶቪየት ኅብረት ሰባት መሪዎችን፣ ጃፓን 21 ጠቅ/ሚኒስትሮችን፣ ጎረቤቷ ደ/ኮሪያ 6 ፕሬዚዳንቶችን አስተናግደዋል። ሞት አይቀርምና ሲሞቱ ልጃቸውን ለልጃቸው አሸጋግረው አልፈዋል። እርሳቸው በበኩላቸው "ታላቁ መሪ"፤"The Great Leader" (በኮሪያኛ *Suryong*) የሚል ቅጽል ተቀጽሎላቸዋል። ከዚያም ባሻገር በሕገ መንግሥት ደረጃ የተቀመጠ የአገሪቱ "ዘላለማዊ ፕሬዚዳንት" ተብለው ተሰይመዋል። የልደት ቀናቸውም ከዓመታዊ አገሪቱ በዓላት እንደ አንዱ በይፋ እንዲከበር ተሰይሟል።

በየአደባባዩ፣ በየታላላቅ ሕንጻዎች፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በምክር ቤት ወዘተ ወዘተ ፎቶግራፋቸውን ከመደበኛ ይዘት እጅግ ከፍ ባለ መጠን እያሳተሙ መስቀል የገጽ ግንባታ ሳይሆን "ከልት"/Cult መፍጠር ነው። አሁን ባለው ይዘት መለስ ዜናዊን ኪም ኤል-ሱንግ ማድረግ ለገዢው ፓርቲም ሆነ ለቤተሰባቸው ክብር አይሆንም። "የመለስ ራእይ" ከሚለው ጀርባም የሚኖረው ይኸው "ዘላለማዊነት" የተመኙለት መሪ እና ኢትዮጵያዊ-ኪም አል ሱንግ የመፍጠር ሐሳብ ነው። ፓርቲው "ራእዩ" በትክክል የገባቸው እና ያልገባቸው፣ ራእዩን የተቀበሉና ያልተቀበሉ፣ የራእዩ ተቃዋሚዎችና ደጋፊዎች በሚል ፍረጃ ውስጥ ለመግባት አፋፍ ላይ ይመስላል። ነገ ማንም ሰው ያለምንም አመክንዮ "ራእዩን ባለመደገፉ ብቻ" ወንጀለኛ ሊባል ይችላል። ኢሕአዴግ የታገለው የፓርቲ ዓላማ ነበረው። መለስም ያንን አይተው ነው የፓርቲው አባል የሆኑት። አሁን ግን መመሪያቸው የመለስ ራእይን መቀበል እና አለመቀበል "ማስቀጠልና አለማስቀጠል" ሆነ ማለት ነው?

አሁን ግን መመሪያቸው የመለስ ራእይን መቀበል እና አለመቀበል "ማስቀጠልና አለማስቀጠል" ሆነ ማለት ነው?

በነገራችን ላይ "ማስቀጠል" የሚለው ቃል ሁሌም ያስፈግገኛል። ቋንቋ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል በሚለው

የሥነ-ቋንቋ ሀ-ሁ እንዳምን ከሚያደርጉኝ ነገሮች አንዱ እንዲህ ያሉት ቃላት ናቸው። "ማስቀጠል" የሚል ግስ ተፈጠረ ማለት ነው? ለነገሩ ሁሉም "አስቀጣይ" ከሆነ ማን "ቀጣይ" ሊሆን ነው? ቃሉን "መገደብ" በሚል ብትተረጉሙት ሁሉም "አስገዳቢ" ከሆነ ማን "ገዳቢ" ሊሆን ነው። ሁሉ ከሆነ ቃልቻ ማን ይሸከማል ስልቻ አለ ያገራችን ሰው። ይቆየን - ያቆየን።

## እየተካሄደ ባለው እልህ አስጨራሽ ጸረ ወያኔ ትግል በግላቸው አንዳችም ነገር ሳያበረክቱ ያገኙትን ሁሉ የሚተቹ ግለሰቦች መስዋእትነት እየከፈለ ያለው ወገን ላይ ከሚሰነዝሩት አፍራሽ አስተያየት እንዲቆጠቡ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ አሳሰቡ

የግንቦት 7 ንቅናቄ ሊ/መንበር ይህን የተናገሩት ዴሞክራሲያዊ ለውጥ በኢትዮጵያ ድጋፍ ድርጅት ኖርዌይ፣ በኦስሎ ከተማ ባዘጋጀውና በክብር እንግድነት በተጋበዙበት፣ በሃገሩ ባህል የገና ገበታ (ዩለ ቡር) እየተባለ በሚጠራው የእራት ግብዣ ላይ ለተገኙት ኢትዮጵያዊያን ነው።

ዶ/ር ብርሃኑ በዚሁ ወቅት እንዳሉት ትግሉን ከፍተኛ መስዋእትነት እዲጠይቅ ያደረገው የኢትዮጵያ ህዝብ ደመኛ ጠላት የሆነው፣ የወያኔ ጥንካሬ ሳይሆን የእኛ ያለ አንዳች ማንገራገር በደልና ውርደትን ለመሸከም አመቺ ሆኖ መገኘት ነው።ይህ ደግሞ ደርግ ትውልድ በማጥፋት ካደረሰው ጥፋት በባሰና በከፋ ሁኔታ በደልና ውርደትን ተሸክመን በዝምታ ወደ መቃብር መውረድን ተቀብለን እንድንኖር ማድረጉ ያመጣብን ጣጣ ነው። ይህ አዙሪት አንድ ቦታ ላይ ካልተሰበረ ደግሞ ግፉና ውርደቱ በባሰ ሁኔታ መቀጠሉ አይቀሬ ነው።

እናም አሉ ዶር ብርሃኑ፣ ዛሬ ጥቂት ጀግኖች ይህን አዙሪት በመስበር ህይወታቸውን ለትግሉ ቤዛ እያደረጉ ባሉበት ወቅት በሞቀ ቤታችን ተቀምጠን ሞራል የሚነኩ እላፊ አስተያየቶችን የምንሰነዝር ሰዎች ራሳችንን ልንመረምር ይገባል ብለዋል።

በማከልም የተለያዩ ግፍና ውርደቶችን በተለያዩ ጊዜያት የሚሞክርብን ዋነኛ ጠላታችን ወያኔ እያለ፣ እርስ በእርስ ለመጠላለፍ የምናደርገው ሽኩቻ የወያኔን ህልውና ከማራዘም ውጪ አንዳችም የሚፈይደው ነገር አለመኖሩን አብራርተዋል።

በሃገራችን ነጻነት፣ ፍትህና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የምንሻ ወገኖች ሁሉ ሌሎች የሚሰሩትን ከመተቸታችን በፊት እኔ ምን ሰርቻለሁ? የምነቅፋቸው ምን ሰርተው ምን ተሳሳቱ? ስህተት ካለ በምን መንገድ በገንቢ ሁኔታ ማረም ይቻላል?የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎችን በማንሳት መመርመር ያስፈልገናል ያሉት ዶ/ር ብርሃኑ ከዚህ ባለፈ ግን በዴሞክራሲ ከለላ የትግሉን እሳት ለማጥፋት፣ የጥፋት ውሃ የሚቸልሱ መሰሪ አድርባዮችን በግልጽ እረፉ፣ በቃችሁ ልንላቸው ይገባል በማለት አስረድተዋል።

ከዚህ ሌላ ዶ/ር ብርሃኑ በዝግጅቱ ላይ የተገኙ ኢትዮጵያዊያን ላነሷቸው ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ምላሽ ከመስጠታቸውም በላይ ከበርካቶች ጋር በግል ተወያይተዋል።

በዚሁ ወቅት የዴሞክራሲ ለውጥ በኢትዮጵያ ድጋፍ ድርጅት ኖርዌይ ሊቀመንበር አቶ ዳዊት መኮንን በበኩላቸው የሚመሩት ድርጅት በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርዓት እዲሰፍን ለሚታገሉ ድርጅቶች ድጋፍ እንደሚሰጥ ገልጸው በዚህ መሰረት በአሁኑ ሰዓት ከሀገር ቤት ለአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)፣ በውጪ ከሚንቀሳቀሱ ደግሞ ለግንቦት ሰባት ድጋፍ እንደሚያደርግ በመጥቀስ በኖርዌይ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የድርጅታቸው አባል በመሆን ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ለማገዝ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አስተላልፈዋል።

## የወያኔው ባህልና ቱሪዝም መሥሪያ ቤት እየታመሰ ነው

የዘረኛውና አምባገነናዊው ወያኔ አገዛዝ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በመስሪያ ቤቱ የወያኔ ሹመኞች መካከል በተነሳ ከፍተኛ ውዝግብ ምክንያት እየታመሰ መሆኑን ሰንደቅ ጋዜጣን በመጥቀስ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ሪፖርት ገለጸ። እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት በወያኔዎቹ ሚንስትር ተብየዎች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ላይ ግራ መጋባትን የፈጠረ ሲሆን ከ 1 ሺህ 800 በላይ የሚሆኑ የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ስራቸውን በአግባቡ ማከናወን እንዳልቻሉ ታውቋል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት የጸቡ ምክንያት የቀድሞ የሶማሌ ክልል ፕሬዝዳንትና ሚኒስትር ዴኤታው ዳውድ መሐመድ የሚኒስትር መስሪያቤቱ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱን ለብልሹ አሰራር አጋልጠውታል በማለት ነቀፌታ በማቅረቡ ነው።

ዘጋቢያችን ሰንደቅ ጋዜጣን በመጥቀስ እንደዘገበው የሁለቱ ሚኒስትሮች አለመግባባት የተቋሙ የማኔጅመንት ሰራተኞች በተሳተፉበት በቅርቡ በተካሄደ ስብሰባ ለመፍታት ቢሞከርም በሚኒስትሮቹ መካከል በተፈጠረ እሰጥ አገባ ሰራተኛው ግራ ተጋብቶ እንደሚገኝ ተገልጿል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ዳውድ መሃመድ አሁን ስለተፈጠረው ችግር ሲጋዜጣው ፤ “ትልቁ የሚያጣላን ነገር የአመራር ችግር ነው። "በማለት መግለጹን ዘጋቢያችን ገልጹዋል።

በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጥቅም ምክንያት ርስ በርስ በመጋጨት ላይ የሚገኙት የዘረኛው ወያኔ ሹማምንት አንደኛው ሌላዉን በመንነተል ተግባር ላይ በስፋት እየገቡ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን በዚህ መስሪያ ቤት በተፈጠረው ችግርም ሚኒሰትር ዴኤታው " ሚኒስትሩ 128 ሺህ ብር ከመስሪያ ቤቱ ሂሳብ ቋት ወጪ በማውጣት ለህክምና ተጠቅሟል።በመመሪያው መሰረት ሚኒስትሮችና ሚኒስትር ደኤታዎች ስንታመም መታከም ያለብን ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ነበር። ነገር ግን ከባህልና ቱሪዝም ፋይናንስ ወጪ በማድረግ አላግባብ ታክሙዋል” በማለት መግለጹን ሪፖርተራችን ገልጿል።

በመስሪያ ቤቱ ውስጥ እያገለገሉ የሚገኙና ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ ወይዘሮ በተፈጠረው ችግር ዙሪያ ለዘጋቢያችን በሰጡት አስተያየት፣ የወያኔ ባለስልጣናት አንዳቸው ከሌላው የሚለዩበት ምንም አይነት ነገር የለም፣ ርስ በርስ የሚናኮሩትም፣ በሚፈጠር የጥቅም ግጭት እንጂ መሰረታዊ በሆነና ለውጥን ሊያመጣ በሚችል ተግባር አይደለም። እናም ከንዲህ አይነቱ ዝቅጠት ልንወጣ የምንችለው የ ስር አት ለውጥ ሲኖር ብቻ ነው። በመሆኑም ሁላችንም ከዚህ ሃበሳ የምንላቀቅበትን መንገድ መቀየስ ይገባናል ብለዋል።

## ሀፍረተ ቢሱ ኢቲቪ የጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማሪያምን ንግግር ቆርጦ አቀረበ

ከሃያ አንድ አመት በላይ የኢትዮጵያን ህዝብ በአደንቋሪ ፕሮፓጋንዳ ሲያሰለች የከረመዉ የኢትዮጵጵያ ቴሌቪዥን ከሰሞኑ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የኤርትራን ብሔራዊ ቡድን አስመልክቶ ከአልጀዚራ ቴሌቪዥን ጋራ ያደረገዉን ቃለምልልስ ዋናዉን ክፍል ቆርጦ ያቀረበ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ምንጮቻችን በላኩልን ዜና ገሉ። በቅርቡ አዲስ አበባ ዉስጥ አገዛዙ የኤርትራና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድኖች የሚያደርጉትን ጨዋታ በገለልተኛ አገር እንዲካሄድ የጠየቀዉን ጥያቄ አስመልክቶ አልጀዚራ ቴሌቪዥን ኃ/ማሪያም ደሳለኝን ጥያቄ ጠይቆ ነበር። ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ጥያቄዉን ሲመልስ አስመራ ዉስጥ የመጫወት ችግር የለብንም ነበር ያለዉ፤ ሆኖም የኢትዮጵጵያ ቴሌቪዥን ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ከአልጀዚራ ጋር ያደረገዉን ቃለምልልስ በአማርኛ ተርጉሞ ሲያቀርብ የእግር ኳስ ጨዋታዉን በተመለከተ ያለዉን ክፍል ቆርጦ ማስቀረቱን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ እጅግ በጣም እንግዳና አሳፋሪ የሆነ የኢቲቪ አሰራር የሚያሳየዉ የጣቢያዉን ምን ያህል ከደረጃ በታች መዉረድና የተራ አሉባልታ ጣቢያ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የወያኔ አገዛዝ በአንድ ማዕከል የሚመራ የመንደር አምባገነኖች ክምር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አገዛዙ የሚወስዳቸዉን እርምጃዎች የአገሪቱ መሪ አለማወቁን ነዉ። ይህ መለስ ዜናዊ ጠ/ሚኒስትር በነበረበት ግዜ የማያታስብ ነገር በአጋጣሚ የሆነ ሳይሆን የህወሀት ፓርቲ ሆን ብሎ የሚሸበርበዉ ተንኮል አካል መሆኑን ብዙዎች ይስማሙብታል።

## ወንጀለኛዉ የወያኔ ፍርድ ቤት አቶ በቀለ ገርባናን አቶ ኦልባና ሌሊሳን በእስራት ቀጣ

የፖለቲካ ፍርድ በመስጠት የሚታወቀዉ የወያኔ ፍርድ ቤት አገዛዙ በሽብረተኝነት ወንጀል ከስሶ አሰርልኝ ብሎ የላከለትን የኦፌዴንና የኦሮሞ ህዝባዊ ኮንግሬስ ከፍተኛ አመራር አባላት የነበሩትን አቶ በቀለ ገርባንና አቶ ኦልባና ሌሊሳን ከሌሎች ሰባት ተከሳሾች ጋር ከስምንት አመት እስከ አስራ ሦስት ዓመት እስር የፈረደባቸዉ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሳበት ድምጽ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋ መምህር፤ የኦፌዴን ም/ል ሊቀመንበርና የመድረክ አመራር አባል የነበሩት አቶ በቀለ ገባ በ8 አመት እስራት የተቀጡ ሲሆን የየኦሮሞ ህዝባዊ ኮንግሬስ ም/ል ሊቀመንበር የነበሩት አቶ ኦልባና ሌሊሳ ደግሞ በአስራ ሦስት አመት እስራት ተቀጥተዋል። ከዚህ በጠጨማሪ በእነዚህ ሁለት የሙብትና የነጻነት ተሟጋቾች መዝገብ የተከሰሱት አቶ አልቤካ ለሚ፤ አቶ አደም ስትቡሳ፤ አቶ ሙሀመድ መሎ፤ ወ/ት ሀና ዋቆ ፤አቶ ደረጀ ከተማ፣ አቶ አዲሱ ምክሬና አቶ ገልገሎ ጎፉ ከሦስት አመት እስከ አስራ ሁለት አመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ተፈርዶባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ አቶ በቀለ እና አቶ ኦልባና ለአራት አመታት ሌሎቹ ተከሳሾች ደግሞ ለሁለት አመታት ህዝባዊ መብታቸው እንዲቀማ ተወስኖባቸዋል።

የፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በተለይ የህዝባዊ መብት እገዳዉን በተመለከተ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዝግጅት ክፍል የጠየቃቸዉ አንድ የህግ ባለሙያ እንደተናገሩት የወያኔ ፍርድ ቤቶች አድርጉ ተብሎ የሚሰጣቸዉን ትዕዛዝ ብቻ የሚፈጽሙ ሮቦቶች ናቸዉ ካሉ በኋላ ፍርድ ቤቱ ከእስራት በተጨማሪ የወሰነዉ የህዝባዊ መብት እገዳ እሳቸዉን ብቻ ሳይሆን የአገዛዙን ማንነት የሚያዉቀዉን ኢትዮጵያዉ ሁሉ እንዳሳቀ ተናግረዋል። ስማቸዉና የሚሰሩበት ቦታ እንዳይጠቀስ የጠየቁን እኚህ የህግ ባለሙያ ምንም አይነት መብት የሌላቸዉን ዜጎች “ህዝባዊ መብታችሁ” ታግዷል ማለት በህዝብና በአገር ላይ መቀለድ ነዉ ብለዋል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ፦** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ፦** በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፦ ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን፡፡ g7radio@ginbot7.org